የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 47
ADDIS ABABA 27th July, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፬/፪ሺ፬ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ ከተማ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ልማት ፕሮጀክት (ክፍል III) ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… **ገጽ ፮ሺ፫፻፸፪**

**CONTENTS**

**Proclamation No.754/2012**

Export-Import Bank of China Loan Agreement for Financing Addis Ababa Deep Wells Water Supply Project (Phase III) Ratification Proclamation. …….Page 6372

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፬/፪ሺ፬

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል ለአዲስ አበባ ከተማ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ልማት ፕሮጀክት (ክፍል III) ማስፈፀሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአዲስ አበባ ከተማ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ልማት ፕሮጀክት (ክፍል III) ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፺፭ ሚሊዮን ፮፻፹ሺ የአሜሪካን ዶላር (ዘጠና አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሺ የአሜሪካን ዶላር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፩ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 754/2012.

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA FOR ADDIS ABABA DEEP WELLS WATER SUPPLY PROJECT (PHASE III)**

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China stipulating that the Export-Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 95,680,000 United States Dollars (ninety five million six hundred eighty thousand United States Dollars) for Addis Ababa Deep Wells Water Supply Project (Phase III) was signed on the 5th day of December 2011;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 28th day of June 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ከተማ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ልማት ፕሮጀክት (ክፍል III) ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፬/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ኢ.ኢ.አ ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፩ የተፈረመው ቁጥር 1420303052011111536 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፺፭ ሚሊዮን ፮፻፹ሺ የአሜሪካን ዶላር (ዘጠና አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሺ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export Import Bank of China Loan Agreement for Financing Addis Ababa Deep Wells Water Supply Project (Phase III) Ratification Proclamation No.754/2012".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. 1420303052011111536 signed on the 5th day of December 2011, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 95,680,000 USD (ninety five million six hundred eighty thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of July, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**